# የወያኔ ውሸት ከሃገራዊ ወደ አለም አቀፋዊ

ከበልጅግ አሊ

የወያኔ ውሸት አገራዊ ይዞታውን ትቶ አለማቀፋዊ ውሸት እየሆነ መምጣቱን ይልተገነዘበ ካለ የአስተሳሰብ ችሎታው የተዛባበት ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የድብቅ እስር ቤት የለም፤ ፖለቲካ እስረኞቸች የሉም ፤ እነ ጺጋዬ ደብተርውን አላሰርኩም ብሎ ሲዘላብድ የነበረው ወያኔ ዛሬ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ግፊት አለም አቀፍ አሸባሪዎች ይገፎ በድብቅ እስርቤቴ አጉሪያለሁ ብሎ እንዲያምን ተደርጎል። ወያኔ መዋሸት ልማዱ መሆኑን የኢትዮጰያ ህዝብ በደንብ አድርጎ ነው የሚያውቀው። ከሀገራችን የሚሰማውማ በጣም ነው የወያኔን ማንነት የሚገልፀው።

በሃገራችን መንግስት አፈናውን በሚያጠናክርበት ጊዜ ህዝቡ በቀልድ መልክ ብሶቱን ይገልጻል። ደርግ ሊውርድ አካባቢ ብዙ ቀልዶች በደርግ ላይ ተነግረዋል። አሁንም በወያኔ ብዙ እየተነገረ ነው። አንድ እውጭ አገር የሚኖር ግለሰብ ወደ ሃገራችን ይሄድና ለእናቱ አንድ በጣም ትልቅ ቴሌቪዥን ገዝቶ ይመለሳል። ከጥቂት አመታት በኋላ ግለሰቡ እንደገና ተመልሶ እናቱን ሊጠይቅ ሲመጣ ቴሌቪዥኑ በትንሽ ተቀይሮ ያገኘዋል። ግለሰቡ ሲፈራ ሲቸር እናቱን ምነው እናቴ ቴሌቪዥኑ አነስብኝ ብሎ ይጠይቃቸዋል። እናትየውም ሲመልሱ «አይ ልጄ ወያኔ በየማታው በዜና ላይ ሲዋሽ ቴሌቪዥኑ ሲሸማቀቅ፤ ወያኔ ሲዋሽ እንደ ገና ሲሸማቀቅ እንደዚህ አነሰ» አሉት ይባላል። ይህ እንግዲህ በቅርብ ከሃገራችን የመጣ ያጫወተኝ ነው።

ለእኔ ወያኔም ይሁን የወያኔ ደጋፊዎች ውሽታሞች ናቸው። ይሉኝታ የሌላቸው ቀጣፊዎች ናቸው። በደርግና በወያኔ መካከል ያለው ልዩነት አንድ ነው። ደርግ የቆሸሸ የውስጥ ልብሱን አውጥቶ ያሳያል ወያኔ ግን ይደብቃል። በቆሻሻነት ግን ሁለቱም ቆሻሻዎች ናቸው። ደርግ አስሮ ገድሎ ይፎክራል እነዚህ ግን አስረው ገድለው ለቀስተኛ ነን ሊሉና ሊቀባዥሩ ይጥራሉ ።

በረከት ስምኦን ታላቁ ውሽታም SAN FRANCISO CHRONICLE የሚባል ጋዜጣ በ APRIL 16/2007 ባወጣው እትሙ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ግርፋት እንደማይደርስባቸው ሲቀላብድ ነበር። ይህ ውሽታም ከዚህ በፊት የድብቅ እስር ቤት የለም ሲል እንደነበረ ግልፅ ነው።

የነፀጋዬ ደብተራውን መታሰር እና ደብዛ መጥፋት ወያኔ ሲክደን አንዳንድ የሰብአዊ ድርጅቶችም ይኸን ጥያቄ አንስተው መጠየቅ ከወያኔ በወቅቱ በጣም ያቃርነናል ስላሉ ዝምተን መርጠው ነበር። ምንም የረባ ግፊት አልተደረገም ነበር። አሁንም የት እንደደረሱ ሁሉም የሰብአዊ ድርጅቶች ሊያነሱት ይገባል። ለአሸባሪዎቹ የዘነበ እውነት ለኢትዮጵያውያኑ ቢያካፋስ ምን አለበት? ሁሉም የፓለቲካ እስረኞች ይፈቱ የሚለው ጥያቄ ሁላችንም ካነሳን ምን አልባት በጥቅም ምክንያት ጆሮው የተደፈነው የምዕራቡ ክፍል ያዳምጠን ይሆናል። ግን ጥያቄያችን በቅርብ በታሰሩት የድርጅት መሪዎች መፈታት ላይ ብቻ ከሆነ ደግሞ በየድብቅ እስር ቤት ውስጥ ያሰራቸው ቆራጥ ኢትዮጵያውያን ተረስተው ቀሩ ማለት ነው።

Posted on www.debteraw.com on 17 April 2007 @ 23:28

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ሌላ የውሸት መረቡን ዘርግቶአል። የምዕተ አመቱን መቀየሪያ በሰፊው ለማክበርና የህዝብ ድጋፍ ያለው ለማስመስል ደፋ ቀና ሲል ይታያል። ይህን ለመስፈፀም ቱባ ቱባ ውሸታሞች ቀጥሮ አሰማርቶአል። በሚሌኒየም ኮሚቴ ተቀጥረው የሚገኙት ውሸታሞች ወያኔ ሚሊኒየሙን ለመደገስ ለምን እንዳሰበ ደብቀው ወያኔን ለኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ዋነኛ ተቆርቋሪ አድርረገው ማቅረብ ይፈልጋሉ። እንደው አንዳንዴ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን ድህረ ገፅ የተመለከትን እንደሆን ስንት የሚያስቅ ነገር ማንበብ ይቻላል። የኢንዲያ ኤንባሲ ሚሌንየም ለማክበር ተባባሪነቱን ገለፀ ይላል ዜና አገልግሎቱ ። የኢትዮጵያ ህዝብ ያልተባበረውን በአል በውጭ ኤንባሲና ከውጭ በሚመጡ ሆዳሞች ሊከበር ነው ማለት ነው? ታዲያ ይህ ሁሉ የፓለቲካ እስረኞች ባሉባት አገር ይህንን በአል እንዴት ነው ህዝቡ ሊያከብር የሚችለው? ይህን ውሸት የተሞላበትን ዝግጅት ማክሸፍና እንደ ግንቦቱ ምርጫ ወያኔ የጠበቀው ሳይሆን ያልጠበቀውን፤ ነገር ግን ህዝቡ የሚፈልገውን ማሳየት ያስፈልጋል። የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ ላይ መስራት አለባቸው። ህዝቡ እንዲህ ጭፍጨፋ በበዛበት እንዴት ተቃውሞውን ለማሰማት ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ማሰብ ያስፈልጋል። እኔ በበኩሌ አንድ የሚቻል ነገር አለ ብዬ አምናለሁ። ህዝቡ ተቃውሞውን ሊያሰማ የሚችለው በምሽት በኡኡታ ቢሆን ወያኔ በምንም ሊቆጣጠረው አይችልም። የኡኡታ ተቃውሞ በዚያ ግዜ ቢዘጋጅ የወያኔ ሴራ ይከሽፋል ሆዳም ይደነግጣል ። የውጭ ጋዜጠኞች ያንን ያራግቡታል። ይህ ታዲያ ሊሰራ ከሚችሉት ውስጥ አንዱ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች ይህንን አስበው ወያኔ ባልመረጠው ህዝብ ድጋፍ እንዳለው ለማሳየት የተጀመረው የሆዳሞች ጥረት ሊከሽፍ የሚችልበት መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ሰሞኑን የወያኔ ሚዲያዎችና የወያኔ ደጋፊዎቹ አንድ ታላቅ ውሸት ጀምረዋል። በውሸቱ ያገሪቱን ኢኮኖሚ አሳብጠው አሳብጠው ያለ የለለ ዕድገት ሰጥተውት ይገኛል። በፕሮፖጋንዳ መሳሪያቸው በመጠቀም አገሪቱ ምንም የኢኮኖሚ ችግር የሌለባት ነች ብለው ሲቀሰቅሱ ይታያሉ። ለእነርሱ የሚታያቸው የራሳቸው ኪስ ማበጥ የአገሪቱዋ ማደግ መስሎ ይታያቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በጣም ችግር ላይ በመሆኑ በቤተሰብ 25 ኪሎ ስንዴ በወር ለመስጠት ወያኔ እየተጣደፈ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ የስራ አጡ ብዛት ስንት መቶኛ (ፐርሰንት) እንደሆነ ወያኔና ደጋፊዎቹ አያነሱም። ምኑ ላይ እንደሆነ እድገቱ ለኔ ግልጽ አደለም። ለኔ ብቻ ሳይሆን ለብዙዎቻችን ግራ የሚጋባን የተደረደረ የቡና ቤት ብዛት ምርትን የሚጨምር ይመስል ኢትዮጵያ ደርሰው የሚመለሱ ሆዳሞች «አገሪቱዋ እንዴት ተሻሽላለች፤ የተከፈቱ አዳዲስ ሆቴሎችን ብዛት በተመለከትከው» ይሉኛል። እንግዲህ ለነርሱ የእድገት መለኪያቸው ጣሪያው ማምሻም እድሜ ነችና ሲጨፍሩ ያደሩበት የቡና ቤት ብዛት ነው ማለት ነው ። በዚያ በኩል ብዙ ቡና ቤት ስለተከፈተ ለነርሱ እድገቱ ይታያቸዋል። ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን ሁኔታው እየከፋ ነው የሄደው እንጂ ምንም መሻሻል አይታይበትም። በአዲስ አበባ መብራት በተራ እየታደለ፤ ውሃ በሳምንት እየተለቀቀ ኢኮኖሚ አደገ የሚባለው ማላገጥ ይመስለኛል።

የወያኔ ደጋፊዎች አሳብን የመግለፅ ነፃነት አለ ብለው ሲቀባጥሩ ይታያሉ። ነጻው ፕረስ ተዘግቶ ምንም እንቅስቃሴ በማያሳይበት በአሁኑ ግዜ እነ ሪፖርተርና እነ አይጋ ፎሩም እንደ ነፃ ፕረስ ለማሳየት የሚሞክሩ አይጠፉም። አዲስ ዘመንም ፤ ኢትዮጵያ ሬዲዮም ፋናንም ጨምሮ ለቱሪስቱ ፈረንጅ እንደነፃ ፕረስ ሊያቀርቡለት ይቻላል። ግን ቱሪሰት ብላ የሚለው አነጋገር ይሰራ እንደሆን እንጂ ማንንም በዚህ አይን ያወጣ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ቅጥፈት አያታልሉንም። የነፃው ፕረስ አባሎች እስር ቤት ውስጥ ናቸው። ነጻው ፕረስ ታስሮአል። የነፃው ፕረስም ሆነ ነፃው ፕረስ አባላት ሊፈቱ ይገባል። ጥያቄያችን አባላቱ ይፈቱ ብቻ ሳይሆን ፕረሱንም እንዲፈታ መጠየቅ ያስፈልጋል።

በሌላው በጣም አሳሳቢ የሆነው ለወጣቱ ውሸት ከማስተማራቸው በላይ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ለወጣቶች ምሳሌ ሆነው ሊታዩ አልቻለሁም። እንዲያውም የሚወራው ቤተመንግስቱ የጫት መቃሚያ መሆኑን ነው። ሌት ተቀን ጫት ይዘው በምርቃና እንዴት አገራችን እንደምትተዳደር አላውቅም። ወያኔ ዕፅን በሃገራችን አብዝቶአል። በውጭ አገር የሚገኙ የወያኔ ደጋፊዎች ይህንኑ ሲያመላልሱ ነው የሚገኙት። ከዚህ የዱርዬዎች መንግስት ከውሸት በስተቀር ምን እንደሚጠበቅ አላውቅም። የሚያሳፍር አይነት ጠባይ ያላቸው የመንግስት መሪዎች ናቸው ያሉን። ለመጪው ትውልድ የሚያስተምሩት ውሸትንና ጎጂ ባህሎችን ነው። ሱሰኝነትን ነው ። ዛሬ ሚሌኒየሙን እንዲያዘጋጁ የተመረጡት በመጠጥ ፍቅር የተነደፉ ናቸው ብሎ በቅርብ ከሃገር የመጡ ግለሰብ አስረድተውኛል። ከህብረተሰቡ ስልተነጠሉ ጭንቀታቸውን በመጠጥ ቢወጡት አይደንቀኝም።

አገራችን ያለችበት ሁኔታ አስከፊ ነው። ውሸትን የተመረኮዘ መንግስት ነው በስልጣን ላይ ያለው። ይህንን ሁሉ ችግር እንዴት ነው የምንወጣው ብለን ማሰብ አለብን። ድርቁ አዲስ አበባ ደርሶአል። ስንዴ እየታደለ ነው። ውሃ በፈረቃ ሆኑዋል። መብራትም እንደዚሁ። ወያኔና ሆዳሞች ተባብረው ሚሌኒየምን ሊደግሱ ነው። የፖለቲካ እስረኞችም እዛው ቃሊቲና በየድብቁ እስር ቤት ውስጥ እየማቀቁ ነው። ሁላችንም ከተባበርን የወያኔን ሚሌኒየም እንደ ግንቦቱ ምርጫ ወያኔ «ወይኔ ባልጀመርኩት» እንዲል እናደርገዋለን። ወያኔ እኛን እየከፋፈለ የቤት ስራ እንደሚሰጠን እኛም ለወያኔ ሚሊኒየምን የሚዋረድበት መድረክ ለማድረግ ከአሁኑ ቅስቀሳው ቢጀመር ጥሩ ነው እላለሁ።

ስለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም

በልጅግ አሊ

Posted on www.debteraw.com on 17 April 2007 @ 23:28

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com